ትብብር

TIBIBIR

Consortium Of Ethiopian Civic Society Organizations (TIBIBIR)

2134 West Highland Avenue, Chicago, IL 60659
Tel: 773 341 8511 - Web: tibibir.org - Email: info@tibibir.org

# ሁሉን አቀፍ የኢትዮጵያ ባለድርሻዎች ጉባዔ

## ከየካቲት ፱ – ፲፪ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.

## በ ሲያትል ዋሽንግተን ይካሄዳል

አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አገር፤ ሕዝባችንም ኢትዮጵያዊ አንድነቱንና ብሔራዊ ስሜቱን እንደያዘ፤ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት በአገር ቤትና በውጭው ዓለም የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተ ጉባኤ ከየካቲት ፱ – ፲፪ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም. (February 16-19, 2018) በ ሲያትል ዋሽንግተን ይካሄዳል። ለዚህ ጉባዔ መሳካት የጉባኤው ተሳታፊ የፖለቲካ ድርጅቶች ያሳዩትን ቀና ትብብርና ቁርጠኝነት እያመሰገነ "የኢትዮጵያ ማሕበረሰብዓዊ ድርጅቶች ትብብር" ተቋም ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቋል።

የዚህ የባለድርሻዎች ጉባዔ ዓቢይ ዓላማ፤ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚታየውን ልዩነት አቻችሎና አጥብቦ በዋና የአገራችን እና የሕዝባችን መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ መግባባትን በመፍጠር፤ እየተካሄደ ያለውን ሕዝባዊ ትግል አቅጣጫ ለማስያዝ እንዲረዳ ታስቦ ነው።

በሌላም በኩል በዲፕሎማሲው መስክ በዓለም መንግስታትና የረድኤት ድርጅቶች ዘንድ የአገራችንን እና የሕዝባችንን መከራና ሰቆቃ የማጋለጡን ዘመቻ በተናጠል ከማድረግ ይልቅ በጋራ ድምጽን ማሰማቱ ተደማጭነቱን ስለሚያጎላው የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርገው በማመን ነው።

በተጨማሪም በሀገራችን ሉዓላዊነትና  በሕዝባችን አንድነት ጽኑ እምነት ኖሯቸው ትግሉን በተናጠል እያካሄዱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማሰባሰብ የጋራ ሕብረት እንዲፈጥሩ በማገዝ መስዋዕትነት እየከፈለ ላለው ሕዝባችን በአስተባባሪ አገራዊ አጀንዳ ላይ በመግባባት የተቀናጀ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችል አስተማማኝ ኃይልና ጥንካሬ ለማጎልበት ነው።

ስለዚህ ይህ በቅርቡ የሚካሄደው የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ ጉባዔ ስኬታማ ውጤት ለማስመዝገብ እስከዛሬ ሲጠየቅና ሲጠበቅ ለነበረው የኅብረት ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በመሆኑም አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አገር፣ ሕዝባችንም ኢትዮጵያዊ አንድነቱንና ብሔራዊ ስሜቱን እንደያዘ፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ይህ በአንድነት ለአንድነት የሚደረገው የሀገር አድን ትግል ወሳኝ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ድጋፉን እንዲሰጥ አበክረን እናሳስባለን። በቀጣይነትም የዚህ ጉባዔ ውጤት ከህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በኋላ ለሚቋቋመው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ምስረታ ቅድመ ዝግጅትና ድልድይ ይሆናል ብለን እናምናለን።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር**
**ጥር ፳፰ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.**